


# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

## የአገልግሎትና ቴክኖሎጂ ክላስተር

## የቅንጅት ስራዎች

## 2018 እቅድ

**ህዳር/ 2018 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**

## ማውጫ

1. መግቢያ ........................................................................ 3

2. ራዕይ፣ ተልዕኮና ዕሴቶች ........................................................ 5

2.1 ራዕይ ........................................................................ 5

2.2 ተልዕኮ........................................................................ 5

3 የዕቅዱ ዓላማ ................................................................... 6

2.1 በክላስተሩ የተቀናጁ ተቋማት ዝርዝር ............................................ 6

2.2 1 ቁልፍ ክላስተር ተቋማት.................................................... 6

2.2.2 ሁለተኛ ደረጃ ተቋማት.................................................... 6

2.2.3 ባለ ዘርፈ ብዙ ክላስተር ተቋማት ........................................... 6

2.3 የአገልግሎትና ቴክኖሎጂ ክላስተር የትኩረት መስክ ................................ 7

3.1 በአገልግሎትና ቴክኖሎጂ ክላስተር የታቀዱ ተግባራት፤ ............................ 7

ግብ 1፡- የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም እና የሰው ሀብት ልማት ማጠናከር፤.................. 7

4.1 ከተግባር አፈጻጸም የሚጠበቁ ውጤቶች.......................................... 12

4.2 የአፈጻጸም አቅጣጫ ............................................................ 12

4.3 የግንኙነት አግባብ ............................................................. 12

4.4 የክትትልና ድጋፍ አግባብ ...................................................... 13

4.5 በተግባር አፈጻጸም የሚያጋጥሙ ችግሮችና መወሰድ ያለባቸው የመፍቴ አቅጣጫዎች.......... 14

5. ማጠቃለያ ...................................................................... 14

6. የድርጊት መረሀ ግብር ........................................................... 15

# ክፍል አንድ

## 1. መግቢያ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለውጡን ተከትሎ በየአመቱ እያስመዘገብን ያለነው ስኬታማ የፍኖተ ብልጽግና ጉዞ አንዱ አካል የሚሆነው አገልግሎትን በማዘመን የማህበረሰብ እርካታ ማረጋገጥ ነው። ለዚህም የመደመር መንግስት ያስቀጣቸውን አቅጣጫ በመከተል የተለያዩ ሴክተሮችን በማቀናጀት ለጋራ የከተማ እድገት የጋራ ቅንጅት እንዴት መፍጠርና ለዘመናዊ ከተማ አስተዳደር ስኬት የሚበጀውን መንገድ የሚያሳይ የቅንጅት ስራዎች ማንዋል በከተማ ተደራጅቶ በሰባት ክላስተር በማደራጀት/ በመደመር ስኬታማ አገልግሎት አሰጣጥን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም መስራት እንዲያስችል እና ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት በማረጋገጥ የማህበረሰቡን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፣የሰው ተኮር ስራዎችን በማስፋት ማህበራዊ ልማትን በማፋጠን የጀመርነውን ስኬታማ የፍኖተ ብልጽግና ጉዞ በማስቀጠል ውጤታማ ስራዎች እንዲሰሩ የሚያስችል ማንዋል ተዘጋጅቶ ወደ ስራ ተገብቷል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከአሁን በፊት እያከናወንን በነበረውን ስኬታማ ጉዞ በማስቀጠል ክፍተትን ለመሙላት የሚያስችል የቅንጅት ስራዎች መሆናቸው ካለፉት ሁለት ዙር የኮሪደር ልማት ስራቻችን በርካታ ልምድ ያገኘንበት በመሆኑ ይሄን በሁሉም ስራዎች ለማምጣት እንዲያስችል በተለየ ትኩረት እየሰራን ነው። በዚሁ መሰረት በየተቋማት ያለው ተልዕኮ በግልና በጋራ ጥምረት መሰራት ያለባቸውን በመለየት እንድንሰራ በማስፈለጉ ከተደራጁት ሰባት ክላስተር አንዱ የሆነው የአገልግከሎትና ቴክኖሎጂ ክናስተር ሲሆን ይሄ ክላስተር የትኩረት ማእከል የሚሆኑ አስር ተግባራትና አራት ዋና ዋና አላፊነት ተሰቶናል።

የአገልግሎት እና ቴክኖሎጂ ክላስተር በጋራ አስራ ሁለት ተቋማትን በማቀፍ የተደራጀ ሲሆን እነዚህን በማቀፍ በተሰጠው አቅጣጫ መሰረት የተለያዩ ተግባራት ያለው የቅዱን አላማ ፣አስፈላጊነት ፣የቅንጅታዊ ስራ ራዕዮ ተልኮና እሴት፣የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባርና ዝርዝር ተግባራት፣የሚጠበቁ ውጤቶች፣የሚያጋጥሙ ችግርና መፍትሔ እንዲሁም የድርጊት መርሀ ግብር ባካተተ መልኩ በሚከተለው መልኩ የቅንጅት እቅዳችን አዘጋጅተናል።

## 2. ነባራዊ መነሻ ሁኔታ

የከተማችን አስተዳደር ባለፉት የለውጥ አመታት ያስመዘገባቸው በርካታ ስኬታማ ስራዎች እንዳሉ ሆኖ በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ አሁንም ከማህበረሰቡ የሚነሱ ችግሮች እንዳሉ ይታወቃ።ይሄንንም ለመፍታት ባለፉት አራት አመታት የተለያዩ ስራዎች ተሰርተዋል ስኬታማ ውጤት አስመዝግበናል።ከተማችንን ወደ ምርጥ ከተሞች ለመቀየር የአገልግሎት አሰጣጡ ላይ የሚታዩ ክፍቶችን በመለየት ሪፎርም የተሰራ ሲሆን አገልግሎቶች/ስራዎች በቴክኖሎጂ እንዲታገዙ በማድረግ ሌብነትና ብልሹ አሰራርን ለመቀነስ የሚያስችል ተግባራት ተከናውኗል።

ለስማር ሲቲ ግንባታ አጋዠ የሚሆንና ለአስቀመጥነው ፍኖተ ብልጽግና ስኬታማ ጉዞ ማሳያ የሆነ ዘመናዊ አገልግሎት አሰጣት በቅርብ የከፈትነው አዲስ መሶብ አገልግሎት ትልቅ ስኬት ተደርጎ በመወሰድ ይህንኑ ለማስፋት የተጀመረው ጥረት ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት ነው።ሰፊ የህዝብ አገልግሎት ያለባቸውን ተቋማት በመለየት አገልግሎቱን ለማዘመን የሚያስችል አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በማልማት እየተሰሩ ያሉ ስራዎች ያመጧቸው ለውጦች ትልቅ ሲሆን ይህን አጠናክሎ ለማስቀጠል የቅንጅት ስራ ወሳኝ ነው።

የሰራተኛው የገቢ አቅምን ለማጠናከርና የኑሮ ውድነትን ለመቋቋም የሚያስችሉ የተለያዩ ድጎማዎች፣ ለአገልግሎት እንዲተጋ የሚያደርጉ ትራንስፖርት እንዲሁም በቅርብ የተደረገው የደሞዝ ጭማሬ ትልቅ አቅም ሲሆን ሰራተኛው ጋር ያለውም የአመለካከት የአቅም ክፍት መሰረት በማድረግ እየተሰጠ ያለው የአቅም ግንባታ ስልጠናና የስራ ቦታውን ምቹ በማድረግ የተጀመረው ጥረት የሚበረታታ ነው።ይሄም የአገልጋይነት መንፈስን በማሳደግ የአገልጋዩን እርካታ እያሳደገ የሚገኝ ነው።

በሌላ በኩል ምንም እንኳን ለዘመናት የተከማቹ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል በተለየ ትኩረት የተሰራው የአገልግሎት ውጤታማነት እና አገልግሎትን በቴክኖሎጂ በማስደገፍ የተሰሩ ስራዎች ውጤት ሰፊ ቢሆንም አሁንም የተሟላ የማህበረሰብ እርካታ ያልፈጠርንና ሌብናትና ብልሹ አሰራርን በምንፈልገው ደረጃ አለማድረሳችን የሚታወቅ ነው።የተለወጠ፣ ለማገልገል ብቁ እና ውጤታማ አገልጋይ ቁጥር እየጨመረ ቢመጣም ዛሬም ቢሆን ለአገልግሎት አሰጣጡ እንቅፋት የሚሆንና በሌብነትና ብልሹ አሰራር ለመክበር ሌት ተቀን የሚሰሩ ሰራተኞችን ቁጥሩ

ቀላል አይደለ። ለሙያው የሚመጥን የተለያዩ ስልጠናዎች አቅሙን የሚገነባ ባለሙያ እንዳለ ሁሉ የአቅም ክፍተት ያለበትም ሰራተኛ ቁጥሩ ቀላል አይደለም። አገልግሎት ፈላጊው ማህበረሰብ እርካታው እያደገ የመጣ መሆኑ በጥሩ ቢወሰድም መንግስት ለመድረስ ከሚያስበው አንጻር ክፍት እንዳለ የማይካድ ነው። በመሆኑም ይሄን የሚቀይር ስራ በቀጣይ ይሄን መቀየር ይጠበቃል።የአገልግሎትና ቴክኖሎጂ ክላስተር ዋናው ተልኮ የሚሆነው የአገልግሎት አሰጣጡን በማዘመን የማህበረሰቡን እርካታ ለማሳደግ በመሆኑ ለዚህ የሚሆኑ የተለያዩ ተግባራት በማቀድ መስራትና የፍኖተ ብልጽግናን ጉዞን በመደመር መንግስት እሳቤ መምራት ውጤት ማስመዝገብ ይኖርብናል።

## 3. ራዕይ፣ ተልዕኮና ዕሴቶች

### 3.1 ራዕይ

በተቋማት መካከል ጠንካራ ቅንጅት ተገንብቶ የከተማውን ልማትና መልካም አስተዳዳር በማረጋገጥ ውጤታማ የሆነ ዘመናዊ አገልግሎት በመስጠት በ2022 ለአፍሪካ ተምሳሌት የምትሆን ከተማ ተገንብቶ ማየት ነው፡፡

### 2.1 ተልዕኮ

የተቋማትን ቅንጅት በማጠናከር ፣የሰው ሀብት አስተዳደር ውጤታማነት በማሳደግ፣የመንግስት አገልግሎቶችን ዲጅታላይዝ በማድረግ፣የአገልግሎት ቅልጥፍናና ተደራሽነትን እና ግልጸኘነትን በመፍጠር የዜጎችን እርካታ ማሳደግ ነው።

### 2.2 እሴቶች

- አገልጋይነትን መላበስ
- ፈጠራና ልህቀት
- ቅልጥፍናና ውጤታማነት
- ግሌፅነትና ተጠያቂነት
- አሳታፊነትና ውጤታማነት
- ቅንጅትና የጋራ መግባባት
- የህግ የበላይነት ማክበር

## 3 የዕቅዱ ዓላማ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር የሚገኙ የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት በቴክኖሎጂና በመረጃ የተደገፈ አሰራርን በመከተል፤ በተቀናጀ መልኩ የሀብትና የጊዜ ብክነትን በማስቀረት የህዝቡን የመልካም አስተዳደርና የአገልግሎት አሰጣጥ ችግሮችን በመቅረፍ ዘመናዊ የአገልግሎት ስርአት መፍጠር ነው።

# ክፍል ሁለት

### 2.1 በክላስተሩ የተቀናጁ ተቋማት ዝርዝር

### 2.2 1 ቁልፍ ክላስተር ተቋማት

- የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ
- የፕላንና ልማት ቢሮ
- የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ
- የአዲስ መሶብ የአንድ ማእከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት መስጫ ተቋም
- የሲቪል ምዝገባና ነዋሪዎች አገልግሎት

### 2.2.2 ሁለተኛ ደረጃ ተቋማት

- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኮሙኒኬሽን ቢሮ
- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ስራዎች ድርጅት
- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ህብረት ስራ ኮሚሽን
- የአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ
- አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ

### 2.2.3 ባለ ዘርፈ ብዙ ክላስተር ተቋማት

- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ
- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሴቶች ህጻናትና ማህበራዊ ቢሮ

## 2.3 የአገልግሎትና ቴክኖሎጂ ክላስተር የትኩረት መስክ

የሰው ሀብት አስተዳደርን ውጤታማነት በማሳደግ፣ የመንግስትን አገልግሎቶችን ዲጂታላይዝ በማደረግ የአገልግሎት ቅልጥፍናን፣ ተደራሽነትን እና ግልጸኝትን በመፍጠር የዜጎችን እርካታ ማሳዳግ ነው።

# ክፍል ሦስት

## 3.1 በአገልግሎትና ቴክኖሎጂ ክላስተር የታቀዱ ዋና ዋና ግቦች አላማና ተግባራት፤

# ግብ 1፡- የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም እና የሰው ሀብት ልማት ማጠናከር፤

### ዓላማ 1. የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም ማሳደግ

ተግባር 1፡- ክፍተትን መሰረት ያደረገ ሰልጣኞችን መለየትና እንዲሰለጥኑ ማድረግ፣

ተግባር 2፡- የተለያዩ አደረጃጀቶች እና በመንግስት ተቋማት የሚገኙ ሰራተኞች በኢትዮ ኮርደስ ስልጠና እንዲወስዱና ሰርቲፋይ እንዲሆኑ መስራት፣

ተግባር 3፡- የማስፈፀም ክፍተትና የአገልግሎት አሰጣጥ ችግሮችን በጥናት መለየት፤

ተግባር 4፡- የተቋማትና ባለሞያዎችን ምዘና ውጤት ተዓማኒነትን ማረጋገጥ

### ዓላማ 2፡- የአደረጃጀት ችግር እና የሰው ሃይል እጥረት ችግሮችን መፍታት

ተግባር 1፡- ከአደረጃጀት የአፈፃፀም ውጤታማነት ጥናት መሰረት በማድረግ ችግሮችን መፍተታት፤

ተግባር 2፡- የከተማ አስተዳደር በሚያስቀምጠው አቅጧጫ መሰረት የሰው ሃይል ማሟላት፤

### ዓላማ 3፡- የተቀማት ምዘናና ብቃት ማከናወን፤

ተግባር 1፡- የብቃት ምዘና ለማከናወን የሚያስችል የተቃምና የሰራተኛ ልየታ ማከናወንና መመዘን፤

ተግባር 2፡- በየተቋማቱ ያለ አመራርና ሰራተኛ ምዘና በአሰራሩ መሰረት እንዲሰራ ማድረግ፤

### ዓላማ 4፡- በየደራጀው ለሚገኙ የመንግስት ሰራተኞች የህብ/ስ/ማህበራት ላይ እንዲደራጁ ማድረግና ድጋፍ መስጠት

ተግባር 1፡- የቤት ልማት ፕሮግራም ላይ በማህበር እንዲደራጁ በማድረግ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፤

ተግባር 2፡- በየተቋማት የገንዘብ ቁጠባና ብድር ማህበራትን ማጠናከርና ማደራጀት፤

ተግባር 3፡- በየተቋማቱ የሸማቾች የህብረት ስራ ማህበራትን ማጠናከርና ማደራጀት፤

ተግባር 4፡- የኢንዱስትሪ እና የግብርና ምርቶችን በተመጠጠኝ ዋጋ በተቋማት በሚዘጋጁ የሸማች ሱቆች ተደራሽ ማድረግ፤

ተግባር 5፡- የሲቨል ሰርቫንቱን የኑሮ ጫና ማቃለል ለሚያስችሉ ሥራዎች ፋይናንስ ማመቻቸት፣

### ዓላማ 5፡- ፐብሊክ ሰርቫንቱ በማህበረሰብ አቀፍ ስፖርትና በስፖርት ለሁሉም እንቅስቃሴ በማሳተፍ ጠንካቱ የተጠበቀ ሲቪል ሰርቫንት መገንባት

ተግባር 1፡- የማህበረሰብ አቀፍ ማስ ስፖርት ፕሮግራም የሠራተኞችን ተሳታፊና ተጠቃሚነት ማሳደግ፤

ተግባር 2፡- በተቋማት ለሚገነቡ የስፖርት ማዕከላትና ማዘውተሪያ ሥፍራዎች ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ፤

## ግብ 2፡- <u>የተቀናጀ ቴክኖሎጂ ልማትና አስተዳደር ማሳደግ</u>

### ዓላማ 1፡- የተቀዋማት አገልግሎቶችን የኦንላይንና ዲጂታላይዜሽን ስራዎችን ማጠናከር፤

ተግባር 1፡- አሁን ስራ ላይ ያሉ የአንድ ማዕከል አገልግሎቶችን ማጠናከር፤

ተግባር 2፡- የቴክኖሎጂ መሰረተ ልማቶችን መከታተልና በቴክኖሎጂ የሚሰጡ አገልግሎቶች ቀጣይነት እንዲኖራቸው ችግሮችን በመለየት መፍታት

ተግባር 3፡- አዳዲስ ወደ ስራ የሚገቡ የአንድ ማእከላት የቴክኖሎጂ ልማትን ማረጋገጥ፤

## ዓላማ 2፡- በአዳዲስ የቴክኖሎጂ ውጤቶች የመንግሥት አገልግሎቶችን ዲጅታላይዜሽን ማሳደግ

ተግባር 1፡- አገልግሎት የሚበዛባቸው እና ለህብረተሰቡ ተደራሽ ሆኑ ስራዎች እና ለሌብነትና ብልሹ አሰራር ምክኒያት የሚሆኑ አገልግሎቶችን በጥናት መለየት፤

ተግባር 2፡- የተለዩትን አገልግሎቶች በራስ አቅም ቴክኖሎጂ በማልማት ፤

ተግባር 3፡- የለሙ ቴክኖሎጂዎችን ወደ ስራ ማስገባትና ውጤታቸውን መከታተል፤

ተግባር 4፡- በወጣት ስብዕና መገንቢያ ማዕከላት ለስታርት አፖች አገልግሎት ዝግጁ ማድረግ፤

ተግባር 5፡- የወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከላት አገልግሎት አሰጣጥ መከታተያ ዳታቤዝ መከታተል፤

ተግባር 6፡- የጉዲፍቻ ለችግር ተጋላጭ ህፃናት እና እድር ምክር ቤት በኦላይን አገልግሎት መስጫ ሲስተም መዘርጋት፤

ተግባር 7፡- አዲስ እና የለሙ ቴክኖሎጂዎችን ድጋፍ፣ ክትትል፣ ቁጥጥር እና የማሻሻል ስራ ተግባራዊ ማድረግ፤

## ዓላማ 3፡- የአንድ ማዕከል አገልግሎት አሰጣጥ ማሳደግ፣

ተግባር 1፡- በየሴክተሩ ያሉ ዲጂታል አገልግሎቶችን መለየት፣

ተግባር 2፡-የተለዩት ዲጅታል አገልግሎቶች ሰርቪስ ካታሎግ እንዲያዘጋጁ ማድረግ፣

ተግባር 3፡- ከአዲስ መሶብ ዲጂታል አገልግሎቶችን እንዲዋሃዱ/API 6/ ማድረግ፣

ተግባር 4፡- አዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግሥት አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ፣

ተግባር 5፡- ወደ አዲስ መሶብ የገቡ አዳዲስ አገልግሎቶች ሙያዊ ድጋፍ/ስልጠና መስጠት፣

## ዓላማ 4፡- ወቅታዊ የሲቪል እና የፋይዳ ምዝገባን ተደራሽነትን ማሳደግ

ተግባር 1፡- የፋይዳ መታወቂያ ሁሉም የአዲስ አበባ ነዋሪና የመንግስት ሰራተኞች እንዲመዘገብ ማድረግ፤

ተግባር 2፡- በልዩ ፍቃድ ምክንያት እረፍት ወስደው የሚመለሱ የመንግስት ሰራተኞች የተከሰተውን ኩነት በወቅቱ አስመዝግበው እንዲመጡ ማድረግ፤

ተግባር 3፡- የወቅታዊ ልደት ኩነት ምዝገባን በህጻናት ማሳደጊያ፣ በህጻናት ማቆያ /Day care/ ስፖርት ፕሮጀክቶች ላይ በተሟላ ሁኔታ እንዲመዘገብ ማድረግ እና የአገልግሎት ቅድመ ሁኔታ ማድረግ፤

ተግባር 4፡- የጉዲፈቻ ኩነት ምዝገባን በህጻናት ማሳደጊያ ቦታዎች በወቅቱ እንዲመዘገቡ ማድረግ፤

ተግባር 5፡- የባይተዋር ሞት ኩነት ምዝገባን በወቅታዊ እንዲመዘገብ ማድረግ፤

ተግባር 6፡-በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ ጤና ተቋማት የሚከሰቱ ልደትና ሞት በወቅቱ እንዲመዘገቡ ማድረግ፤

ተግባር 7፡- በአዲስ አበባ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች የልደት ሰርተፍኬት እንዲኖራቸው ማድረግና ለምዝገባ ቅድመ ሁኔታ ማድረግ፤

ተግባር 8፡- በዘላቂ ማረፍያ ከቀብር በፊት የሞት ምዝገባ እንዲደረግ ማድረግ፤

## ግብ 3፡- <u>የህዝብ ግንኙነት የመረጃ ሽፋን ጥራትና ተደራሽነት ማሳደግ</u>

### ዓላማ 1፡- ጥራት ያለው የአገልግሎት አሰጣጥ መረጃን ተደራሽነት ማሳደግ፤

ተግባር 1፡- ወቅታዊ የአገልግሎት አሰጣጥ መረጃዎችን በሚዲያዎች ለህብረተሰቡ ተደራሽ ማድረግ፤

ተግባር 2፡- ውስብስብ እና ማብራሪያ የሚያስፈልጋቸው የአገልግሎት አሰጣጥ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ፤ የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎችን በመጋበዝ ለህብረተሰቡ ዝርዝር ማብራሪያ እንዲሰጡ ማድረግ፤

ተግባር 3፡- የተቋማትን መልካም ተሞክሮዎች እና ውጤታማ የአገልግሎት አሰጣጥ ሂደቶችን በዶክመንተሪ እና በፕሮግራም ቀረጻ ለሌሎች አርአያ እንዲሆኑ ማስተዋወቅ፤

ተግባር 4፡- በአገልግሎት አሰጣጥ እና ቴክኖሎጂ ዙሪያ የሚሰራጩ የሀሰት መረጃዎችን በመከታተል ማጥራትና ትክክለኛ መረጃ መስጠት፤

## ዓላማ 2፡- የአገልግሎት አሰጣጥ ክፍተቶችን በምርመራ መደገፍ፤

ተግባር 1፡- በተቋማት የአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚታዩ ጉድለቶችን እና የህዝብ ቅሬታዎችን መሰረት በማድረግ የምርመራ (Investigative) ስራዎችን መስራት እና ክፍተቱን መሙላት፤

ተግባር 2፡- ከተቋማት እይታ ያመለጡ፤ ነገር ግን የህዝብ ቅሬታ የሆኑ የአገልግሎት አሰጣጥ እና የመልካም አስተዳደር ችግሮችን መለየት፤ ተቋማቱ መልሰው እንዲያዩት እና እንዲያርሙትና ስርዓት እንዲዘረጉ የማሳወቅ ስራ መስራት፤

## ዓላማ 3፡- የህዝብ ተሳትፎን እና የግብረ-መልስ አሰራር ስርዓትን ማሳደግ

ተግባር 1፡- በአገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ የህዝብ አስተያየት የሚሰበሰብበት ዲጂታል አሰራር ስርዓት በመዘርጋት፤ የህዝቡን እርካታ ደረጃ በየጊዜው መገምገምና ለውሳኔ ሰጪ አካል ሪፖርት ማቅረብ፤

ተግባር 2፡- ማህበረሰብ አቀፍ የውይይት መድረኮችን በማዘጋጀት እና በቀጥታ ስርጭት በማስተላለፍ፤ ነዋሪዎች ከተቋማት መሪዎች ጋር ፊት ለፊት ተገናኝተው ችግሮቻቸውን እንዲያነሱ ማመቻቸት፤

ተግባር 3፡- በማህበራዊ ሚዲያ እና በስልክ ጥሪ ማዕከል የሚመጡ የህዝብ ጥቆማዎችን መተንተን እና ለሚመለከታቸው አካላት ማድረስ፤

ተግባር 4፡- የኑሮ ውድነትን ለማረጋጋት የሚሰሩ ስራዎችን በተመለከተ የህዝብ አስተያየት ቅኝት በመስራት የተሰሩ ስራዎችን በተለያዩ የኮሙኒኬሽን አግባቦች ለህብረተሰቡ መረጃን ተደራሽ ማድረግ።

# ክፍል አራት

## 4.1 ከተግባር አፈጻጸም የሚጠበቁ ውጤቶች

### 4.1.1 ከአጭር ጊዜ አንጻር

- የአገልግሎት አሰጣጡን ቀልጣፋና ውጤታማነት ማሳደግ፤
- የሰራተኛውን አቅም በማሳደግ ለቦታው የሚመጥን ሰራተኛ መፍጠር/መገንባት፤
- የማህበረሰቡን ንቃለ ህሊና በማሳደግ ለአገልግሎት አሰጣጡ የህብረተሰቡን ድርሻ ማሳደግ፤
- ምቹ የስራ አካባቢን በመፍጠር የሰራተኛውን ተጠቃሚነት የሚያሳድጉ አደረጃጀቶች በመፍጠር የኢኮኖሚ ችግሩን በመፍታት የኑሮ ደረጃው ማሳደግ፤
- የሚሰሩ ስራዎችን በህዝብ ግንኙነት ስራዎች ማጀብ በአገልግሎት አሰጣጡ ያሉ ሁኔታዎችን ለህብረተሰብ ማሳወቅ፤

### 4.1.2 ከመካከለኛ ጊዜ አንጻር

- ሌብነትና ብልሹ አሰራርን መቀነስ፤
- አዳዲስ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የአገልግሎቱን ተደራሽነት ማሳደግ፤/
- በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚታዩ ክተቶችን በመድፈን የማህበረሰቡን እርካታ ማሳደግ፤
- በአጠቃላይ በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ ያሉ የአደረጃጀት ክፍተቶችን በመለየትና በማረም ሪፎርሙን በማጠናከር ክፍተትን መሰረት ያደረገ ተቋም ግንባታ ስራዎች በመስራት ብቃትን መሰረት ያደረገ ሰው ሀብት ስምሪትን በማረጋገጥ ብዝሃነትና አካታችነትን በማስከበር የአገልጋይነት መንፈስን በማጠናከር የተገልጋዩን እርካታ የሚያሳድግና ወቅቱን የሚመጥን ዘመናዊ አገልግሎት በመስጠት ልምድ የሚቀሰምበት ከተማ መገንባት ይሆናል።

## 4.2 የአፈጻጸም አቅጣጫ

- እቅድ በጋራ ማዘጋጀት፤
- ተልኮዎች ላይ ጊዜ ወስዶ በመወያየት ግልጽነት መፍጠር፤
- በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት ተግባራት እንዲገመገሙ የሚያስችል ሪፖርቶች በተቋም ተገምግሞ እንዲመጣና በጋራ እንዲታይ ማደስረግ
- ወቅቱን የጠበቀ የስራ ግምገማ ማካሄድና የቀጣይ አቅጣጫ ማስቀመጥ በቀጣይ ግንኙነት የተግባር አፈጻጸሙ ከመገምገሙ በፊት በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት የተከናወኑ ተግባራት አስቀድሞ መገምገም፤
- በተግባር አፈጻጸም ወደ ውጤታማ ያልሆነ ተቋም የመደገፍና ክፍተቱን ለመሙላት ማገዝን በማስቀደም ለውጥ የማያመጣ ከሆነ ተጠያቂ ማድረግ፤

## 4.3 የግንኙነት አግባብ በተመለከተ

- በወሩ የመጨረሻ ሳምንት የቴክኒክ ኮሚቴው በመገናኘት ስራዎችን ይገመግማል።
- በወሩ የመጨረሻ ሳምንት የመጀመሪያ ቀን የባለሙያዎች ግንኑነት በማድረግ ሪፖርት ይጠመራል።
- እንደ አስፈላጊነቱ በማየት የሚጠሩ ስብሰባዎች ይኖራሉ፤

## 4.4 የክትትልና ድጋፍ

- በእቅዱ መሰረት ወደ ስራ መገባቱን መከታተል እና ያጋጠሙ ችግሮችን መፍታት፤
- የተግባር እንቅስቃሴ ያሉበትን ደረጃ በመፈተሽ ውጤታማ እንዲሆኑ በቅንጅት መምራት፤
- ወቅቱን የጠበቀ ሪፖርት በመመልከትና በመገምገም ውጤታማነቱን ማረጋገጥ፤

## 4.5 በተግባር አፈጻጸም ወቅት የሚያጋጥሙ ችግሮችና የሚወሰዱ መፍቴዎች ፤

### 4.5.1 የሚያጋጥሙ ችግሮች፤

- በእኩል ደረጃ ለተግባሩ ትኩረት ያለመስጠት፤
- ተግባራትን በወቅቱ ሪፖርት አለመላክና አለመገምገም፤
- የሚጠበቀው ውጤት ላይ ትኩረት አድርጎ ያለመስራት፤

### 4.5.2 የሚወሰዱ መፍቴዎች፤

- ሁሉም አመራር ስራውን ሲጀምር በተገቢው ባለቤት መሆኑን መግባባት ላይ መድረስ፤
- የድርጊት መርሃ ግብር ቀድሞ በማስቀመጥ ተግባራት ወቅቱን ጠብቀው እንዲገመገሙ ማድረግና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ፤
- ሁሉም ተቋም ውጤት ለማምጣጥና ውጤታማ አገልግሎት ለማረጋገጥ መትጋት እንዳለበት በበቂ ደረጃ መግባባትና በየጊዜው ውጤቱን በመገምገም ስራን መምራት፤

## ማጠቃለያ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በከተማች እየተመዘገቡ ያሉ ውጤታማ የአገልግት አሰጣጥን በማጠናከር የማህበረሰቡን እርካታ ለማሳደግ በመንግስት የተለየ ትኩረት የሚመራው ተግባር እንደመሆኑ በሁሉም ደረጃ የተጠናከረ ስራ መስራት ሚያስችል ቅንጅታዊ አሰራር በመፍጠር ወጥ መመሪያ በማዘጋጀት የሚጠበቁ ውጤቶች ባመላከተ መሰረት አቅጣጫ የተሰጠ ሲሆን በዚሁ መሰረት በአገልግሎትና ቴክኖሎጂ ክላስተር የተደራጀ ሁላችን በጋራ በመጠናከር ውጤታማ ለመሆን መስራት ተቀዳሚ ተግባር አድርገን እንሰራለን በዚህም ተቋማችንና ከተማችን የአገልግሎትና ቴክኖሎጂ ተግባር አፈጻጸምን ውጤታማ ለማረጋገጥ ከላይ በዝርዝር ያስቀመጥነው እቅድ ላይ በበቂ ሁኔታ በመነጋገር መግባባት ላይ የደረስን ሲሆን በክላስተሩ የሚከናወኑ ተግባራት በሚመለከታቸው አባላቱ ጠንካራ ጥረት እንዲሁም ከሌሎች ክላስተር ጋር የምንሰራቸውን ለክላስተራቸውና ለተቋማት በማሳወቅ ውጤታማነቱን እናረጋግጣለን።

| ተ.ቁ | በቅንጅት ለመስራት የታቀዱ ተግባራት | መለኪያ | ለተግባራቱ የተሰጠ ክብደት | መነሻ ዕቅድ | የ2018 በጀት ዓመት ኢላማ | የየሩብ ዓመት ዕቅድ | | | | ውል ተቀባይ (ፈፃሚ ተቋም) | ውል ሰጪ (ትብብር ፈላጊ) | የሚጠበቅ ውጤት | | የክትትልና ግምገማ አግባብ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት | | | የአጭር ጊዜ ውጤት (Output) | የመካከለኛ ጊዜ ውጤት (Outcome)፣ ለማሳካት ያቀድነው ዓላማ | |
| | **1. የአገልግሎት እና ቴክኖሎጂ ክላስተር** | | | | | | | | | | | | | |
| 1 | **ስትራቴጂክ ግብ 1፡-** 1. የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም እና የሰው ሀብት ልማትን ማጠናከር(44%) | | | | | | | | | | | | | |
| 1.1 | **አላማ1፦ የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም ማሳደግ**(20%) | | | | | | | | | | | | | |
| 1.1.1 | **ተግባር1፡-** ክፍተትን መሰረት ያደረገ ሰልጣኞችን መለየትና እንዲሰለጥኑ ማድረግ | በቁጥር | 5% | 0 | 5000 | | 1500 | 2000 | 1500 | የአዲስ አበባ ከተማ አመራር አካዳሚ | የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ | ክፍተትን መሰረት ያደረገ አቅም መገንባት | ብቃት ያለው ሲቪል ሰርቫንት መገንባት | |
| 1.1.2 | **ተግባር2፡-** በመንግስት ተቀዋማት የሚገኙ ሰራተኞች በኢትዮ ኮደርስ ስልጠና እንዲወስዱና ሰርቲፋይ እንዲሆኑ መስራት | በቁጥር | 3% | | 50000 | | | 25000 | 25000 | ፐብሊክ ስርቪሰ የስውሃብት ልማት ቢሮ | የአዲስ አበባ ከተማ ኢኖቬሽንና ቴከኖሎጀ ልማት ቢሮ | የቴክኖሎጂ አቅምን ማጠናከር | የቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ቁጥር ማሳደግ | |
| 1.1.3 | **ተግባር3፡-** የተለያዩ አደረጃጀቶች በኢትዮ ኮደርስ ስልጠና እንዲወስዱና ሰርቲፋይ እንዲሆኑ መስራት | በቁጥር | 3% | 0 | 50000 | | | 25000 | 25000 | የአዲስ አበባ ከተማ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ እና የህንረተሰብ ተሳትፎና ማስተባበሪያ ኮምሽን | ኢኖቫሽን ትከኖሎጀ ልማትቢሮ | የወጣጦች የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ማሳደግ | በቴክኖሎጂ ብቁ የሆነ ወጣቶቾን መፍጠር | |

| | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1.1.4 | **ተግባር4፡-** የማስፈፀም ክፍተትና የአገልግሎት አሰጧጥ ችግሮችን በጥናት መለየት | በቁጥር | 4% | | 2 | | | 1.00 | 1 | | የአዲስ አበባ ከተማ አመራር አካዳሚ | የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ | አገልግሎት አሰጣጡ ያለበትን ደረጃ ማወቅ | ውጤታማ አገልግሎት በመስጠት እርካታን ማሳደግ | |
| 1.1.5 | **ተግባር5፡-** የተቋማትና የባለሙያዎችን ምዘና ውጤት ተዓማኒነትን ማረጋገጥ | በመቶኛ | 5% | | 100% | | | | | 100 % | የአዲስ አበባ ከተማ ፕላን ልማት ቢሮ ፣ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ከንቲባ | የክላስተር ተቋማት | ሁሉም ሰራተኛና ተቋማት በምዘና እንዲያልፉ ማድረግ | ተአማኒ የሆነ የሰራተኛና ተቋም ምዘናን ማካሄድ | |
| 1.2 | **አላማ2፦ የአደረጃጀት ችግር እና የሰው ሃይል እጥረት ችግሮችን መፍታት** (4%) | | | | | | | | | | | | | | |
| 1.2.1 | **ተግባር1፡-** ከአደረጃጀት የአፈፃፀም ውጤታማነት ጥናት መሰረት በማድረግ ችግሮችን መፍታት | በመቶኛ | 2% | | 100 | | | | 100 | 100 | ፐብሊክ ስርቪሰ የስውሃብት ልማት ቢሮ | የክላስተር ተቋማት | የአደረጃጀት ክፍተቶችን በመለየት ማስተካከል | ውጤታማ አደረጃጀት በመፍጠር አገልግሎቱን ተደራሽ ማድረግ | |
| 1.2.2 | **ተግባር2፡-** የከተማ አስተዳደር በሚያስቀምጠው አቅጣጫ መሰረት የሰው ሃይል ማሟላት | በመቶኛ | 2% | | 100 | | | | 100 | 100 | ፐብሊክ ስርቪሰ የስውሃብት ልማት ቢሮ | የክላስተር ተቋማት | የሰው ሀይል ክፍተትን መሙላት | በተማላ የሰው ሀይል አገልግሎት መስጠት | |
| 1.3 | **አላማ3፡- የተቀማት ምዘናና ብቃት ማረጋገጥ** (4%) | | | | | | | | | | | | | | |
| 1.3.1 | **ተግባር1፡-** የብቃት ምዘና ለማከናወን የሚያስችል የተቋምና የሰራተኛ ልየታ ማከናወንና መመዘን | በመቶኛ | 2% | | **100** | | | | | 100 | **የአዲስ አበባ ከተማ አመራር አካዳሚ እና ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን** | ፐብሊክ ስርቪሰ የስው ሃብት ልማት ቢሮ | **ምዘና ማከናወን** | **ብቃት ያለው የሰው ሀይል ማደራጀት** | |
| 1.3.2 | **ተግባር2፡-** በየተቋማቱ ያለ አመራርና ሰራተኛ ምዘና በአሰራሩ መሰረት እንዲሰራ ማድረግ | በመቶኛ | 2% | | **100** | | | | | 100 | **የአዲስ አበባ ከተማ አመራር አካዳሚ እና ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን** | ፐብሊክ ስርቪሰ የስው ሃብት ልማት ቢሮ | **ምዘና ማከናወን** | **ብቃት ያለው የሰው ሀይል ማደራጀት** | |

| | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1.4 | **አላማ 4፡- በየደራጃው ለሚገኙ የመንግስት ሰራተኞች የህብ/ስ/ማህበራት ላይ እንዲደራጁ ማድረግና ድጋፍ መስጠት(12%)** | | | | | | | | | | | | | |
| 1.4.1 | **ተግባር1፡-** በሚቀርበው እንደራጅ መሰረት የቤት ልማት ፕሮግራም ላይ በማህበር እንዲደራጁ በማድረግ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ | በመቶኛ | 2% | | 100% | 0% | 0% | 100 % | 100 % | ፐብሊክ ስርቪሰና የሰው ሃብት ልማት ቢሮ | ህበረት ስራ ኮሚሽን | የቤት አቅርቦት ችግር ለመፍታ መሰረት መጣል | የቤት ተጠቃሚነትን በማረጋገጥ የኑሮ ጫናን መቀነስ | |
| 1.4.2 | **ተግባር2፡-** በየተቋማት የገንዘብ ቁጠባና ብድር ማህበራትን ማጠናከር | በመቶኛ | 2% | | 100% | 0% | 0% | 100 % | 100 % | ፐብሊክ ስርቪሰና የሰው ሃብት ልማት ቢሮ | ህበረት ስራ ኮሚሽን | ለስራ ምቹ ሁኔታ መፍጠር | | |
| 1.4.3 | **ተግባር3፡-** በየተቋማት የሸማቾች የህብረት ስራ ማህበራትን ማደራጅት ከመንግስት ተቀዋማት የእንድራጅ ፍላጎት ማስባሰብና ማድራጅት | በቁጥር | 2% | | 100% | 0% | 0% | 100 % | 100 % | ፐብሊክ ስርቪሰና የሰው ሃብት ልማት ቢሮ | ህበረት ስራ ኮሚሽን | የተጠናከረና አሰራርን የተከተሉ ማህበራትን ማጠናከር | የኑሮ ውድነት ማረጋጋት | |
| 1.4.4 | **ተግባር4፡-** አዲስ የሸማቾች የህብረት ስራ ማህበራትን ማደራጅት | በመቶኛ | 2% | | 100% | 0% | 0% | 100 % | 100 % | ፐብሊክ ስርቪሰና የሰው ሃብት ልማት ቢሮ | ህበረት ስራ ኮሚሽን | የጋራ ችግሮች ለመፍታ በማህ ማደራጀት | ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ | |
| 1.4.5 | **ተግባር5፡-** የሲቪል ሰርቫንቱን የኑሮ ጫና ማቃለል ለሚያስችሉ ሥራዎች ፋይናንስ ማመቻቸት፣ | በብር | 2% | | 1ቢ | | 05ቢ | 250 ሚ | 250 ሚ | ፐብሊክ ስርቪሰና የሰው ሃብት ልማት ቢሮ | አአ ንግድስራዎች ድርጅት | የግብርናና ኢንዱስትሪ ምርቶች የዋጋ መርጋጋት ይፈጠራል | ኑሮ ግሸበት እቀንሳለን | |

| | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1.4.6 | ተግባር 6 የኢንዱስትሪ እና የግብርና ምርቶችን በተመጠጠኝ ዋጋ ተቋማት ባመቻቹት የሸማች ሱቅ ለሲቨል ሰርቫንቱን ተደራሽ ማድረግ | በመቶኛ | 2% | | 100% | 100 % | 100 % | 100 % | 100 % | አአ ንግድ ስራዎች ድርጅት ህበረት ሰራ ኮሚሽን | ፐብሊክ ሰርቪሰ የሰውሃብት ልማት ቢሮ | ኑሮ ይርጋጋል | የተረጋጋ ግብይት እንዲኖር ያደርጋል | |
| 1.5 | አላማ5፡- ፐብሊክ ሰርቫንቱ በማህበረሰብ አቀፍ ስፖርትና በስፖርት ለሁሉም እንቅስቃሴ ማሳተፍ(4%) | | | | | | | | | | | | | |
| 1.5.1 | **ተግባር1:-** የማህበረሰብ አቀፍ ማስ ስፖርት ፕሮግራም የሠራተኞችን ተሳታፊና ተጠቃሚነት ማሳደግ | **በቁጥር** | 2% | | 120,000 | 20,000 | 40,000 | 40,000 | 20,000 | የክላስተሩ አባላት | የአዲስ አበባ ከተማ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ | ፐብሊክ ሰርቫንቱ በስፖርት ተሳታፊና ተጠቃሚ ማድረግ | ህብረተሰቡን በአግባቡ የሚያገለግል ጡናማና ንቁ ሰራተኛ መፍጠር | |
| 1.5.2 | **ተግባር2፡-** በተቋማት ለሚገነቡ የስፖርት ማዕከላትና ማዘውተሪያ ሥፍራዎች ክትትልና ድጋፍ ማድረግ | በመቶኛ | 2% | | 100% | | | 100 % | 100 % | የአዲስ አበባ ከተማ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ | የአዲስ አበባ ከተማ አመራር አካዳሚ | የስፖርት ማዘውተሪያ ቦታዎች በወቅቱ እንዲጠናቀቁ ማድረግ | ጤናው የተጠበቀ ብቃት ያለው ሰልጣኝ ማፍራት | |
| 2 | **ግብ 2 የተቀናጀ ቴክኖሎጂ ልማትና አስተዳደርን ማዕስለ(36%)** | | | | | | | | | | | | | |
| 2.1 | **አላማ 1፡- የተቋማት አገልግሎቶችን የኦንላይንና ዲጂታላይዜሽን ማጠናከር(5%)** | | | | | | | | | | | | | |
| 2.1.1 | **ተግባር1፡-** አሁን ስራ ላይ ያሉ የአንድ ማእከል አገልግሎቶችን ማጠናከር፤ | በመቶኛ | 2% | | 75% | | | | 75% | የአዲስ አበባ ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስ የሰው ሀብት ልማት ቢሮ | የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት | የለሙ የአንድ ማዕከል የአገልግሎት መስጫ ማዕከላት ማድረግ | በተገልጋዮ ህብረተሰብ አመኒታ የተጣለበት ተቋም መገንባት | |

| | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2.1.2 | **ተግባር2፡-** የቴክኖሎጂ መሰረተ ልማቶችን መከታተልና በቴክኖሎጂ የሚሰጡ አገልግሎቶች ቀጣይነት እንዲኖራቸው ችግሮችን በመለየት መፍታት | **በመቶኛ** | 1% | | 80% | | | 40% | 40% | ኢኖቫሽን ትክኖሎጂ ልማትቢሮ | **የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት** | **ጥራት ያለው የቴክኖሎጂ አገልግሎት መገንባት** | **የተሟላ የቴክኖሎጂ አገልግሎት መስጠት** | |
| 2.1.3 | **ተግባር3፡-** አዳዲስ ወደ ስራ የሚገቡ የአንድ ማእከላት የቴክኖሎጂ ልማትን ማረጋገጥ፤ | **በመቶኛ** | 2% | | 60% | | | 60% | | ኢኖቫሽን ትክኖሎጂ ልማትቢሮ እና የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት | የአዲስ አበባ ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስ የሰው ሀብት ልማት ቢሮ | **የተቴክኖሎጂ ውጤቶችን ወደ ስራ ማስገባት** | **የተሟላ የቴክኖሎጂ አገልግሎት መስጠት** | |
| 2.2 | **አላማ2፡- በአዳዲስ የቴክኖሎጂ ውጤቶች የመንግሥት አገልግሎቶችን ዲጅታላይዜሽን ማሳደግ**(14%) | | | | | | | | | | | | | |
| 2.2.1 | **ተግባር1፡-** አገልግሎት የሚበዛባቸው እና ለህብረተሰቡ ተደራሽ የሆኑ ስራዎች እና ለሌብነትና ብልሹ አሰራር ምክኒያት የሚሆኑ አገልግሎቶችን በጥናት መለየት፤ | **በቁጥር** | 2% | | 1 | | | | 1 | የክላስተሩ ተቋማት | የአዲስ አበባ ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስ የሰው ሀብት ልማት ቢሮ | **የሌብነትና ብልሹ አስራርን ለመቀነስ የሚያስችሉ አሰራሮችን ማስቀመጥ** | **ሌብነትንና ብልሹ አሰራርን የሚጠየፍ ትውልድ መፍጠር** | |
| 2.2.2 | **ተግባር2፡-** የተለዩትን አገልግሎቶች በራስ አቅም ቴክኖሎጂ በማልማት፤ እንዲመሩ ማድረግ፤ | **በመቶኛ** | 2% | | 50% | | | | 50% | የአዲስ አበባ ከተማ ኢኖቫሽን ትክኖሎጂ ልማት ቢሮ | የአዲስ አበባ ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስ የሰው ሀብት ልማት ቢሮ | **የሌብነትና ብልሹ አስራርን ለመቀነስ የሚያስችሉ አሰራሮችን ማስቀመጥ** | **ሌብነትንና ብልሹ አሰራርን የሚጠየፍ ትውልድ መፍጠር** | |
| 2.2.3 | **ተግባር3፡-** የለሙ ቴክኖሎጂዎችን ወደ ስራ ማስገባትና ውጤታቸውን መከታተል፤ | **በመቶኛ** | 2% | | 100% | | | 100 % | 100 | የአዲስ አበባ ከተማ ኢኖቫሽን ትክኖሎጂ ልማት ቢሮ | **የክላስተሩ ተቋማት** | **ተግባራትን በቴክኖሎጂ ማስደገፍ** | **ዘመናዊ አገልግሎት ማሳለጥ** | |

| | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2.2.4 | **ተግባር4፡-** በወጣት ስብዕና መገንቢያ ማዕከላት ለስታርት አፖች አገልግሎት ዝግጁ ማድረግ | **በቁጥር** | 2% | | 3 | | | 1 | 2 | የአዲስ አበባ ከተማ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ | **የአዲስ አበባ ከተማ ኢኖቫሽን ትክኖሎጀ ልማት ቢሮ** | **ወጣት ማእከልት በቴክኖሎጂ እንዲ ደራጁ ማድረግ** | **ሁሉም ወጣት ማእከላት በቴክኖሎ ጂ እንዲደራ ጁ ማድረግ** | |
| 2.2.5 | ተግባር5፡- የወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከላት አገልግሎት አሰጣጥ ዳታቤዝ መከታተል፤ | **በቁጥር** | 2% | | 2 | | | 1 | 1 | **የአዲስ አበባ ከተማ ኢኖቫሽን ትከኖሎጀ ልማት ቢሮ** | **የአዲስ አበባ ከተማ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ** | **በተጠናከረ የክትትል ድጋፍ ስራ የወጣቱን ስብዕና ይገነባል** | **ስብዕናው የተገነባ አምራች ሃይል መፍጠር** | |
| 2.2.6 | **ተግባር6፡-** የጉዲፍቻ ለችግር ተጋላጭ ህፃናት እና እድር ምክር ቤት በኦላይን አገልግሎት መስጫ ሲስተም መዘርጋት፣ | **በመቶኛ** | 2% | | 50% | | | | 50% | **የአዲስ አበባ ከተማ ኢኖቫሽን ትከኖሎጀ ልማት ቢሮ** | **ሴቶች፣ህፃና ት እና ማህበራዊ ጉዳይ** | **ሲስተም መዘርጋት** | **ታአማኒነ ት ያለው መረጃ ለመሰብሰ ብ** | |
| 2.2.7 | **ተግባር7፡-** አዲስ እና የለሙ ቴክኖሎጂዎችን ድጋፍ፣ ክትትል፣ ቁጥጥር እና የማሻሻል ስራ ተግባራዊ ማድረግ | በመቶኛ | 2% | | 100% | | | | 100 % | **የአዲስ አበባ ከተማ ኢኖቫሽን ትከኖሎጀ ልማት ቢሮ** | የአዲስ አበባ ከተማ አመራር አካዳሚ | አገልግሎቱን በቴክኖሎጂ ማስደገፍ | ዘመናዊ አሰራርን ማጠናከር | |
| 2.3 | **አላማ3፡- የአንድ ማዕከል አገልግሎት አሰጣጥ ማሳደግ፣**(5%) | | | | | | | | | | | | | |
| 2.3.1 | **ተግባር1፡-** በየሴ ክተሩ ያሉ ዲጂታል አገልግሎቶችን መለየት፣ | በመቶኛ | 1% | | 40% | | | 40% | | የከተማ ሴክተር ተቋማት | የአዲስ አበባ ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስ የሰው ሀብት ልማት ቢሮ | **የተቴክኖሎጂ ውጤቶችን ወደ ስራ ማስገባት** | **የተሟላ የቴክኖሎ ጂ አገልግሎ ት መስጠት** | |
| 2.3.2 | **ተግባር2፡-** የተለዩት ዲጅታል አገልግሎቶች ሰርቪስ ካታሎግ እንዲያዘጋጁ ማድረግ፣ | በመቶኛ | 1% | | 40% | | | 40% | | የከተማ ሴክተር ተቋማት | የአዲስ አበባ ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስ የሰው ሀብት ልማት ቢሮ | **የተቴክኖሎጂ ውጤቶችን ወደ ስራ ማስገባት** | **የተሟላ የቴክኖሎ ጂ አገልግሎ ት መስጠት** | |

| | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2.3.3 | **ተግባር3፡-** ከአዲስ መሶብ ዲጂታል አገልግሎቶችን እንዲዋሃዱ/API 6/ ማድረግ፣ | በመቶኛ | 1% | | 40% | | | 40% | | የከተማ ሴክተር ተቋማት ፣ኢኖቨሽን ቴክኖሎጂ ቢሮ እና AI | የአዲስ አበባ ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስ የሰው ሀብት ልማት ቢሮ | **የተቴክኖሎጂ ውጤቶችን ወደ ስራ ማስገባት** | **የተሟላ የቴክኖሎጂ አገልግሎት መስጠት** | |
| 2.3.4 | **ተግባር4፡-** አዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግሥት አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ፣ | በመቶኛ | 1% | | 40% | | | 40% | | **የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት** | የአዲስ አበባ ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስ የሰው ሀብት ልማት ቢሮ | **የተቴክኖሎጂ ውጤቶችን ወደ ስራ ማስገባት** | **የተሟላ የቴክኖሎጂ አገልግሎት መስጠት** | |
| 2.3.5 | **ተግባር5፡-** ወደ አዲስ መሶብ የገቡ አዳዲስ አገልግሎቶች ሙያዊ ድጋፍ/ስልጠና መስጠት፣ | በቁጥር | 1% | | 600 | | | 300 | 300 | የአዲስ አበባ ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስ የሰው ሀብት ልማት ቢሮ | **የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት** | **በተቴክኖሎጂ አጠቃቅም ብቃታቸው የተረጋገጠ ባለሙያዎችን መፍጠር** | **የተሟላ የቴክኖሎጂ አገልግሎት መስጠት** | |
| 2.4 | **አልማ4፡- ወቅታዊ የሲቪል እና የፋይዳ ምዝገባን ተደራሽነትን ማሳደግ**(12%) | | | | | | | | | | | | | |
| 2.4.1 | **ተግባር1፡-** የፋይዳ መታወቂያ ሁሉም የአዲስ አበባ ነዋሪና የመንግስት ሰራተኞች እንዲመዘገብ ማድረግ፤ | መቶኛ | 2% | | 100% | 0% | 50% | 75% | 90% | የህብረተሰብ ተሳትፎና በጎፈቃድ ቢሮ እና ፐብሊክ ሰርቪስ ቢሮ | ሲቪል ምዝገባ እና የነዋሪነት አገልግሎት ኤጀንሲ | በዲጂታል ሲስተም ተመዝግቦ የታወቀ ዜጋ መኖር | ዘመናዊ የአገልግሎት አሰጣጥና የዳበረ ቁጥጥር ስርዓት መዘርጋት | |
| 2.4.2 | **ተግባር2፡-** በልዩ ፍቃድ ምክንያት እረፍት ወስደው የሚመለሱ የመንግስት ሰራተኞች የተከሰተውን ኩነት በወቅቱ አስመዝግበው እንዲመጡ ማድረግ፤ | መቶኛ | 2% | | 100% | 0% | 0% | 75% | 100 % | ፐብሊክ ሰርቪስ ቢሮ | ሲቪል ምዝገባ እና የነዋሪነት አገልግሎት ኤጀንሲ | ተደራሽ የሆነ ወቅታዊ የኩነት ምዝገባ ስርዓት መኖር | አለም አቀፍ መርህን መሰረት ያደረገ ምዝገባ ስርዓት መተግበር | |

| | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2.4.3 | **ተግባር3፡-** የወቅታዊ ልደት ኩነት ምዝገባን በህጻናት ማሳደጊያ፣ በህጻናት ማቆያ /Day care/ ስፖርት ፕሮጀክቶች ላይ በተሟላ ሁኔታ እንዲመዘገብ ማድረግ እና የአገልግሎት ቅድመ ሁኔታ ማድረግ፤ | መቶኛ | 2% | | 100% | 0% | 0% | 75% | 100 % | ሴቶች ህጻናትና ማህበራዊ ቢሮ ፣ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ እና ፐብሊክ ሰርቪስ ቢሮ | ሲቪል ምዝገባ እና የነዋሪነት አገልግሎት ኤጀንሲ | ተደራሽ የሆነ ወቅታዊ የኩነት ምዝገባ ስርዓት መኖር | አለም አቀፍ መርህን መሰረት ያደረገ ምዝገባ ስርዓት መተግበር | |
| 2.4.4 | **ተግባር4፡-** የጉዲፈቻ ኩነት ምዝገባን በህጻናት ማሳደጊያ ቦታዎች በወቅቱ እንዲመዘገቡ ማድረግ | መቶኛ | 2% | | 100% | 0% | 0% | 75% | 100 % | ሴቶች ህጻናትና ማህበራዊ ቢሮ፣ | ሲቪል ምዝገባ እና የነዋሪነት አገልግሎት ኤጀንሲ | ተደራሽ የሆነ ወቅታዊ የኩነት ምዝገባ ስርዓት መኖር | አለም አቀፍ መርህን መሰረት ያደረገ ምዝገባ ስርዓት መተግበር | |
| 2.4.5 | **ተግባር5፡-** የባይተዋር ሞት ኩነት ምዝገባን በወቅታዊ እንዲመዘገብ ማድረግ፤ | መቶኛ | 1% | | 100% | 0% | 0% | 75% | 100 % | ሴቶች ህጻናትና ማህበራዊ ቢሮ፣ | ሲቪል ምዝገባ እና የነዋሪነት አገልግሎት ኤጀንሲ | ተደራሽ የሆነ ወቅታዊ የኩነት ምዝገባ ስርዓት መኖር | አለም አቀፍ መርህን መሰረት ያደረገ ምዝገባ ስርዓት መተግበር | |
| 2.4.6 | **ተግባር6፡-** በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ ጤና ተቋማት የሚከሰቱ ልደትና ሞት በወቅቱ እንዲመዘገቡ ማድረግ፤ | መቶኛ | 1% | | 100% | 85% | 85% | 95% | 100 % | **ጤና ቢሮ** | ሲቪል ምዝገባ እና የነዋሪነት አገልግሎት ኤጀንሲ | ተደራሽ የሆነ ወቅታዊ የኩነት ምዝገባ ስርዓት መኖር | አለም አቀፍ መርህን መሰረት ያደረገ ምዝገባ ስርዓት መተግበር | |
| 2.4.7 | **ተግባር7፡-** በአዲስ አበባ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች የልደት ሰርተፍኬት እንዲኖራቸው ማድረግና ለምዝገባ | መቶኛ | 1% | | 100% | 85% | 90% | 95% | 100 % | **ትምህርት ቢሮ** | ሲቪል ምዝገባ እና የነዋሪነት አገልግሎት ኤጀንሲ | ተደራሽ የሆነ ወቅታዊ የኩነት ምዝገባ ስርዓት መኖር | አለም አቀፍ መርህን መሰረት ያደረገ ምዝገባ ስርዓት መተግበር | |

| | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ቅድመ ሁኔታ ማድረግ፤ | | | | | | | | | | | | |
| 2.4.8 | **ተግባር8፡- በዘላቂ ማረፍያ ከቀብር በፊት የሞት ምዝገባ እንዲደረግ ማድረግ፤** | መቶኛ | 1% | **0%** | 100% | **0%** | **0%** | **100%** | 100% | **የከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ቢሮ** | ሲቪል ምዝገባ እና የነዋሪነት አገልግሎት ኤጀንሲ | ተደራሽ የሆነ ወቅታዊ የኩነት ምዝገባ ስርዓት መኖር | አለም አቀፍ መርህን መሰረት ያደረገ ምዝገባ ስርዓት መተግበር | |
| 3 | **ግብ 3 የህዝብ ግንኙነት የመረጃ ሽፋን ጠራትና ተደራሽነት (20%)** | | | | | | | | | | | | |
| 3.1 | **አላማ1፡- በቴክኖሎጂ የተደገፈ ጥራት ያለው የአገልግሎት አሰጣጥ መረጃን ተደራሽነት ማሳደግ(8)** | | | | | | | | | | | | |
| 3.1.1 | **ተግባር1፡- ወቅታዊ የአገልግሎት አሰጣጥ መረጃዎችን በሚዲያዎች ለህብረተሰቡ ተደራሽ ማድረግ፤** | በመቶኛ | 2 | | 100% | | | 100% | 100% | አዲስ ሚድያ ኔትዎርክ እና ኮሚዩኒኬሽን ቢሮ | ፐ/ሰ/ሰ/ሃ/ል/ቢሮ | **በይዘት ስራዎች፤ የህዝብ ግንዛቤ ይፈጠራል።** | መረጃ ያገኛና መብቱን የሚያውቅ ማህበረሰብ ይፈጠራል፤ ግልፀኝነት ይሰፍናል፤ | |
| 3.1.2 | **ተግባር2፡-** ውስብስብ እና ማብራሪያ የሚያስፈልጋቸው የአገልግሎት አሰጣጥ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ፤ የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎችን በመጋበዝ ለህብረተሰቡ ዝርዝር ማብራሪያ እንዲሰጡ ማድረግ፤ | በመቶኛ | 2 | | 100% | | | 100% | 100% | የክላስተር ተቋማት | አዲስ ሚድያ ኔትዎርክ እና ኮሚዩኒኬሽን ቢሮ | **በይዘት ስራዎች፤ የህዝብ ግንዛቤ ይፈጠራል።** | መረጃ ያገኛና መብቱን የሚያውቅ ማህበረሰብ ይፈጠራል፤ ግልፀኝነት ይሰፍናል፤ | |

| | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 3.1.3 | **ተግባር3፡-** የተቋማትን መልካም ተሞክሮዎች እና ውጤታማ የአገልግሎት አሰጣጥ ሂደቶችን በዶክመንተሪ እና በፕሮግራም ቀረጻ ለሌሎች አርአያ እንዲሆኑ ማስተዋወቅ፤ | በቁጥር | 2 | | 2 | | | 1 | 1 | አዲስ ሚድያ ኔትዎርክ | የክላስተር ተቋማት | **በይዘት ስራዎች፤ የህዝብ ግንዛቤ ይፈጠራል።** | መረጃ ያገኛና መብቱን የሚያውቅ ማህበረሰብ ይፈጠራል፤ ግልፀኝነት ይሰፍናል፤ | |
| 3.1.4 | **ተግባር4፡-** በአገልግሎት አሰጣጥ እና ቴክኖሎጂ ዙሪያ የሚሰራጩ የሀሰት መረጃዎችን በመከታተል ማጥራትና ትክክለኛ መረጃ መስጠት፤ | በመቶኛ | 2 | | 100% | | | 100 % | 100 % | አዲስ ሚድያ ኔትዎርክ እና ኮሚዩኒኬሽን ቢሮ | ፐ/ሰ/ሰ/ሃ/ል/ቢሮ | **በይዘት ስራዎች፤ የህዝብ ግንዛቤ ይፈጠራል።** | መረጃ ያገኛና መብቱን የሚያውቅ ማህበረሰብ ይፈጠራል፤ ግልፀኝነት ይሰፍናል፤ | |
| 3.2 | **አላማ 2፡- የአገልግሎት አሰጣጥ ክፍተቶችን በምርመራ መደገፍ፤**(7) | | | | | | | | | | | | | |
| 3.2.1 | **ተግባር1፡-** በተቋማት የአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚታዩ ጉድለቶችን እና የህዝብ ቅሬታዎችን መሰረት በማድረግ የምርመራ (Investigative) ስራዎችን መስራት እና ክፍተቱን መሙላት፤ | በመቶኛ | 4 | | 100% | | | 100 % | 100 % | አዲስ ሚድያ ኔትዎርክ | ፐ/ሰ/ሰ/ሃ/ል/ቢሮ | ችግሮች ይለያሉ፤ በተለዩ ክፍተቶች የእርምት እርምጃ ይወሰዳል፤ | በተቋማት ውስጥ ተጠያቂነት ይሰፍናል፤ የአገልግሎት እርካታ ይጨምራል | |

| | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 3.2.2 | **ተግባር2፡- ከተቋማት ዕይታ ያመለጡ፤ ነገር ግን የህዝብ ቅሬታ የሆኑ የአገልግሎት አሰጣጥ እና የመልካም አስተዳደር ችግሮችን መለየት፤ ተቋማቱ መልሰው እንዲያዩት እና እንዲያርሙትና ስርዓት እንዲዘረጉ የማሳወቅ ስራ መስራት፤** | በመቶኛ | 3 | | 100% | | | 100 % | 100 % | አዲስ ሚድያ ኔትዎርክ እና ኮሚዩኒኬሽን ቢሮ | ፐ/ሰ/ሰ/ሃ/ል/ቢሮ | ችግሮች ይለያሉ፤ በተለዩ ክፍተቶች የእርምት እርምጃ ይወሰዳል፤ | በተቋማት ውስጥ ተጠያቂነት ይሰፍናል፤ የአገልግሎት እርካታ ይጨምራል | |
| 3.3 | **አላማ3፡- የህዝብ ተሳትፎን እና የግብረ-መልስ አሰራር ስርዓትን ማሳደግ(5)** | | | | | | | | | | | | | |
| 3.3.1 | **ተግባር1፡- በአገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ የህዝብ አስተያየት የሚሰበሰብበት ዲጂታል አሰራር ስርዓት በመዘርጋት፤ የህዝቡን እርካታ ደረጃ በየጊዜው መገምገምና ለውሳኔ ሰጪ አካል ሪፖርት ማቅረብ፤** | በቁጥር | 2 | | 1 | | | | 1 | አዲስ ሚድያ ኔትዎርክ እና ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ቢሮ | ፐ/ሰ/ሰ/ሃ/ል/ቢሮ | በአገልግሎት ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችን በመቀበል እንዲፈታ ይሰራል፤ | በአሰራር ስርዓት ግልጽነትና ተጠያቀቂነት ይፈጠራል፤ | |
| 3.3.2 | **ተግባር2፡- ማህበረሰብ አቀፍ የውይይት መድረኮችን በማዘጋጀት እና በቀጥታ ስርጭት በማስተላለፍ፤ ነዋሪዎች ከተቋማት መሪዎች ጋር ፊት ለፊት ተገናኝተው ችግሮቻቸውን እንዲያነሱ ማመቻቸት፤** | በቁጥር | 1 | | 2 | | | 1 | 1 | አዲስ ሚድያ ኔትዎርክ እና ኮሚዩኒኬሽን ቢሮ | የክላስተር ተቋማት | በአገልግሎት አሰጧጥ ላይ የማህበረሰብ ንቃተ ህሊና ይዳብራል፤ | መብቱን የሚያቀቅና የሚያስከብር ማህበረሰብ ይፈጠራል፤ | |

| | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 3.3.3 | **ተግባር3፡-** በማህበራዊ ሚዲያ እና በስልክ ጥሪ ማዕከል የሚመጡ የህዝብ ጥቆማዎችን መተንተን እና ለሚመለከታቸው አካላት ማድረስ፤ | በመቶኛ | 1 | | 100% | | | 100 % | 100 % | አዲስ ሚድያ ኔትዎርክ እና ኮሚዩኒኬሽን ቢሮ | የክላስተር ተቋማት | በአገልግሎት ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችን በመቀበ+K63 +M63 | በአሰራር ስርዓት ግልጽነትና ተጠያቀቂነት ይፈጠራል፤ | |
| 3.3.4 | **ተግባር4፡-** የኑሮ ውድነትን ለማረጋጋት የሚሰሩ ስራዎችን በተመለከተ የህዝብ አስተያት ቅኝት በመስራት የተሰሩ ስራዎችን በተለያዩ የኮሙኒኬሽን አግባቦች ለህብረተሰቡ መረጃን ተደራሽ ማድረግ። | በቁጥር | 1 | | 4 | | | 2 | 2 | ኮሚዩኒኬሽን ቢሮ | የክላስተር ተቋማት | መረጃዎችን በማሰባሰብ መለየትና ችግሮችን ይፈታል፤ | የተቋማት ገጽታ በመገንባት የህብረተሰብ አመኔታን ማሳደግ፤ | |
| | **ድምር** | | 100 | | | | | | | | | | | |